# ዳግም አሲምባ
# በመላ-አገሪቱ በአዲስ አበባ

ጀኔራል ሱናሚ

አሲምባ-አሲምባ ምንጊዜም አሲምባ
የማይበርድ የጀግኖች የትግል አምባ
የሚደመስስ አፈር ድሜ የሚያስገባ
መጥቆ ወጣ እንደ ንሥር ባዲስ አበባ
ሕዝብን እፎይ ሊያሰኝ ሊጠርግ እንባ።

ጠላት ሊደመስስ ነፃ ሊያወጣ
ሊጠራርግ የወያኔን ጣጣ ፈንጣጣ።
አገር ሊያድን ክልልን ሊያጠፉ
ሁሉን ሊሰበስብ ሊያስተባብር በይፋ።
የተራበውን ሊያበላ የተጠማውን ሊያጠጣ
ችግረኛውን ሊረዳ ስለምንም ሊያመጣ

ተቀጣጠለ አሉ ዳግም አሲምባ
በመላ-ኢትዮጵያ ከአምባ እስከ አምባ
ከመንደር እስከ መንደር
ከደብር እስከ ደብር
በጠቅላላው በአገሪቱ ምድር

ለእናት አገር የተሰዋችሁ
ለውድ ሕዝባችን የተቀሰፋችሁ
ለኢትዮጵያዊነት የሞታችሁ
ለባንዲራዋ የተዋደቃችሁ የተሰዋችሁ
በግፍ የታሰራችሁ
ሆን ተብሎ ገደል የተጣላችሁ

በፋሽስት በዘረኞች የተገደላችሁ
ተነሱ ሁላችሁም ትፈለጋላችሁ
ለውድ አገራችሁ ተጋዳይ የሆናችሁ።
ክርስቶስ መቃብርን አሸንፎ አርጓል
እናንተም ፈንቅሉ እንበል እልል አልል
የማይቀረውን የዳግም አሲምባን ድል

የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ ይበልህ
መሪህን አሲምባን አገኘህ።